# ጋዜጣዊ መግለጫ

አሜሪካ ኤምባሲ

አዲስ አበባ — ለተጨማሪ መረጃ በ 011-130-7033 ይደውሉ

2012/33 — ድረ ገጽ፡ http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ መንግስት የአርብቶ አደሩን ተጋላጭነት የመቋቋም ብቃት ለማሻሻልና ገበያን ለማስፋፋት የሚያስችል አዲስ ፕሮግራም ይፋ አደረገ

ታህሳስ 9 ቀን 2005 ዓ.ም. አዲስ አበባ፡- የአሜሪካ መንግስት በአፋር፣ ኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች የሚገኙ ከ250,000 በላይ ቤተሰቦችን ተጠቃሚ የሚያደርግ አዲስ የአምስት አመት ፕሮግራም በዛሬው ዕለት ይፋ አደረገ፡፡ ፕሮግራሙ በድርቅ ከተጎዱና ከአርብቶ አደር የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተገኘውን የአስር አመት ልምድ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) "የአርብቶ አደር አካባቢዎች ለችግር ተጋላጭነትን የመቋቋም ብቃት ማሻሻልና ገበያን ማስፋፋት-ፕራይም" በእንግሊዝኛው "Pastoralist Areas Resilience Improvement and Market Expansion- PRIME" በሚል መጠሪያ አዲስ ይፋ ያደረገው ፕሮግራም ፣ በአርብቶ አደሩ ኑሮ ላይ እየጨመረ የመጣውን ጫና ለማቃለል የታለመ ሲሆን ፤ በአሜሪካ ፕሬዚዳንት አነሳሽነት የፊድ ዘ ፊውቸር እና የዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ፕሮግራሞች የጀመሩትን እንቅስቃሴ የሚደግፍ ነው ፡፡ የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ዲሬክተር ዴኒስ ዌለር ንግግር ባደረጉበት ይፋዊ የመክፈቻ ሥነ ስርአት ላይ ፤ የግብርና ሚንስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ጌታሁን ፣ እንዲሁም የፌደራልና የክልል መንግስታት ባለስልጣናት፣ የግሉ ዘርፍ ተወካዮችና አገር በቀልና ዓለም አቀፍ የፕሮግራሙ አስፈጻሚ አጋሮች ተገኝተዋል፡፡

ፕራይም ፕሮጀክት በየጊዜው የአርብቶ አደሩ ማኅበረሰብና ቤተሰብ ደህንነትን የሚፈታተነው የአየር ሁኔታና የገበያ እክልን የመቋቋም ብቃት በዘላቂነት ለማሻሻል የሚያስችል ነው፡፡በተመሳሳይ ሁኔታም ፕራይም በርካታ ቤተሰቦች ከአርብቶ አደር የኑሮ ዘይቤ በመላቀቅ፣ ኑሮአቸውን አርብቶ አደር ባለሆነ ዘይቤ ለመምራት የሚያደርጉትን የሽግግር ጥረት ይደግፋል፡፡

ፕራይም የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ገበያ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት እንዲጨምር ፣ ማኅበረሰቦች በየጊዜው ከሚለዋወጠው የአየር ንብረት ለውጥ ጋር በቀላሉ የመላመድ አቅም እንዲያጎለብቱና የምግብ ዋስትናን እንዲያሳድጉ ፣ አማራጭ የኑሮ ዘይቤዎችን ለማሻሻል የሚያስችሉ የክህሎቶች ሽግግርን ማለትም፡- ማንበብና መጻፍ፣ መሰረታዊ የሂሳብ ስሌት ፣ ለቅጥር የሚያበቁ መሰረታዊ ክህሎቶች፣ የሥራ ፈጠራና የሙያ ስልጠናን ያበረታታል፡፡ እንዲሁም ፕራይም የፖሊሲ ጥናቶችንና የእውቀት ሽግግር ሥርዓትን በማበረታታት ፣ በክትትልና ግምገማ ላይ የተመሰረተ የአርብቶ አደሮች ልማት በምሥራቅ አፍሪካ እንዲጎለብት እገዛ ያደርጋል፡፡

ይህ የ52 ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክት በሚርሲ ኮር አስተባባሪነትና በዓለም አቀፍና አገር አቀፍ አጋሮች አማካኝነት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡እነዚህ ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ አጋሮች ኬር፣ ኪሜትሪካ ፣ኤስ ኦ ኤስ ሳህል፣ ፓስቸራሊስት ከንሰርን፣ ሐሮማያ ዩንቨርሲቲ፣ የአፋር የተቀናጀና ዘላቂ ልማት ማኅበር እና ኤጅድ ኤንድ ችልድረን ፓስቸራሊስት አሶሴሽን ናቸው፡፡

የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ዲሬክተር ዴኒስ ዌለር በመክፈቻው ሥነ ስርዓት ላይ ባደረጉት ንግግረ "ፕራይም በየጊዜው የሚከሰቱ ቀውሶችን ለመቋቋም ፣ የአርብቶ አደሮችን ኑሮ እንዲሁም የቤተሰቦቻቸውንና የማኅበረሰቡን ደህንነት ለማሻሻል ፣ የእንሰሳት ገበያውን እምቅ አቅም ለኢትዮጵያ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስኬት ጠንካራ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ታልሞ ፈርጀ ብዙና ተደጋጋፊ በሆነ አሰራር የተቀረጸ ነው" በማለት ተናግረዋል፡፡

###